ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ Since 1991

# መለእክተ ኢሰመጉ

አንደኛ አመት ቁጥር አንድ ህዳር 2012 ዓ/ም



ከፍ ያለ ስም

ቀለም

ተመዘኑ

ሰዋዊ

ለጥፋት የህዝብን ስሜት ማነሳሳት

# ሕዝበ ውሳኔ እና የሕግ ማዕቀፉ በኢትዮጵያ

C = NEBE

# ርእሰ አንቀጽ

**ኢሰመጉ**

## «እነሆ በረከት!»

ጤና ይስጥልን የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ አባላትና ደጋፊዎች፤ የድርጅታችንን ልሳን «መልዕክተ ኢሰመጉ» በበይነ መረብ አማካይነት ለንባብ በማብቃታችን ልባዊ ደስታ ይሰማናል፡፡ ኢሰመጉ ያለፈበት ውጣ ውረድ ሁሉ ነጸብራቅ የሆነው የድርጅቱ ልሳን ከሁለት ዓመታት በኋላ ዛሬም በአባላትና ባልደረቦች ቀና ትብብር ዳግም ነፍስ ዘርቷል፡፡ በ1997 ዓ.ም ከተካሄደው ምርጫ በኋላ የኢሕአዴግ መንግሥት ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የሚታገሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለማሽመድመድ የወሰዳቸውን የሕግ ሽፋን የተላበሱ እርምጃዎች ተከትሎ የኢሰመጉ ዐቅም በእጅጉ ተመናምኖ ሕልውናው ፈተና ላይ ወድቆ መቆየቱ አይዘነጋም፡፡

የሲቪክ ማኅበራት ቁጥር ዐዋጅ 621/2001 ባስከተለበት ከፍተኛ የገቢ ዕቀባ ምክንያት ኢሰመጉ በነበረው ውሱን የገንዘብ ዐቅምም ቢሆን ሕልውናውን አስጠብቆ ለመቆየት ከወሰዳቸው አስገዳጅ እርምጃዎች መካከል ዋነኛው በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹን መዝጋትና ሠራተኞቹን መቀነስ ነበር፡፡ በባንክ የሚገኘው ገንዘቡ በመታገዱ ምክንያት የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹን በመቀነሱ ሥያሜውን «ከኢሰመጉ» ወደ «ሰመጉ» ለመለወጥ ተገድዶ ነበር፡፡ ከድርጅቱ የሥያሜ ለውጥ ጋር የልሳኑም ሥያሜ ተለውጦ «መልዕክተ ሰመጉ» ተብሎ በወረቀት ጋዜጣ ሲታተም ቆይቷል፡፡

ከ2010ዓ.ም ወዲህ በሐገራችን እየሠፈነ ከመጣው ፖለቲካዊ ለውጥ ጋር ተያይዞ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን አሽመድምዶ የነበረው ሕግ በዐዋጅ 1113/2011 በመሻሩ፤ ድርጅታችንም ሥራውን የማከናወንና ሀብት የማፈላለግ ነጻነት በአንጻራዊነት በመጎናጸፉ በጅግጅጋ፣ በጋምቤላና በመቀሌ አዳዲስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ለመክፈት እንዲሁም በቀድሞ ሥያሜው «ኢሰመጉ» ተብሎ ለመጠራት በቅቷል፡፡ ዛሬ ለንባብ ያበቃነው ልሳንም ሥያሜው ወደ «መልዕክተ ኢሰመጉ» የተመለሰው በዚሁ አግባብ ነው፡፡

አሁን ያለንበት የፖለቲካዊ ለውጥ ዘመን ከሰብዓዊ መብቶች መከበር አንጻር አያሌ ተስፋዎችና ሥጋቶች ይዞ የመጣ ነው፡፡ በዐሥር ሺዎች የሚቆጠሩ የፖለቲካ እሥረኞች መፈታታቸው፣ በተለምዶ «ማዕከላዊ» ተብሎ የሚጠራውን እሥር ቤት ጨምሮ በልዩ ልዩ ሥውር ማሠቃያ ሥፍራዎች ይፈጸም የነበረውን ግፍ መንግሥት በይፋ በማመን ወንጀለኞችን ለሕግ ማቅረብ መጀመሩ፣ ለአፈና መሣሪያነት ሲውል የቆየውን የጸረ ሽብር ዐዋጅ ለማማሻሻል ፈቃደኛ መሆኑ ወዘተ. ተስፋ ሰጪ የለውጡ ትሩፋቶች ናቸው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ የዜጎችን ሞትና ከመኖሪያ ቀዬ መፈናቀል የሚያስከትሉ በየአካባቢው የሚቀሰቀሱ ብሔር ተኮር ግጭቶች፣ የወጣቶች ኢ-መደበኛ አደረጃጀቶች፣ «በጎበዝ አለቃ» የሚታዘዙ የታጠቁ ኃይሎች መፍላት፣ ጥፋት ፈጽሞ በሕግ ተጠያቂ ያለመሆን፣ የኑሮ ውድነትና የኢኮኖሚው አለመረጋጋት የሚፈጥረው ቀቢጸ ተስፋ ወዘተ. ትልቅ ሥጋት የጋረጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በክልል የመደራጀትና የማንነት ጥያቄዎችም በአግባቡ የሚስተናገዱበት የሕግና የፖለቲካ መደላድል በቶሎ ካልተበጀ እስካሁን ካየናቸው ችግሮች የባሰ አስከፊ አደጋ ሊከተል እንደሚችል ምልክቶች እየተስተዋሉ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር መንግሥት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማኅበረሰቡ እንዲሁም ሁሉም ዜጋ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት፣ ሰላምና ዴሞክራሲ የሰፈነባት፣ ሰብዓዊ መብቶች የሚከበሩባት ኢትዮጵያን የመፍጠር ትልም እውን ይሆን ዘንድ ሁሉም የሚጠበቅበትን ድርሻ ይወጣ ዘንድ እናሳስባለን፡፡

ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የቆመው ኢሰመጉም በዚህ ዐውድ ውስጥ ሆኖ ነው ዓላማውን ለማሳካት በመሥራት ላይ የሚገኘው፡፡ ድርጅታችን ዓላማዎቹን ለማስፈጸም ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ በልሣኑ አማካይነት ለአባላቱ፣ ለደጋፊዎቹ፣ ከሰብዓዊ መብቶች ጋር ተያያዥነት ባላቸው መስኮች ላይ ለተሠማሩ የመንግሥት አካላትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ መልዕክቶቹን ማሠራጨት ነው፡፡

ስለሆነም፣ የመልዕክቶቻችን ማሠራጫ የሆነው ልሳን ቀጣይነት ይኖረው ዘንድ አባላትና ደጋፊዎቻችን ለኅትመት የሚሆኑ ጽሑፎችን በማቅረብ፣ በሚታተሙ ጽሑፎችና አጠቃላይ አቀራረብ ላይ ገንቢ ኂስ በመስጠት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጉ ዘንድ በበይነ መድረክ ሲቀርብ የመጀመሪያው የሆነውን እትም «እነሆ በረከት!» በማለት እንጋብዛለን፡፡

## መልእክተ ኢሰመጉ

### አሳታሚ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

### የዝግጅት ክፍሉ ባልደረቦች

ብንያም አባተ
ዳን ይርጋ
ሱራፍኤል ግርማ
ጥበቡ ኃይሉ
ገላውዲዮስ ግሩም

### የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ
ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7
የቤት ቁጥር= 112/37
ስልክ ቁጥር =0118685706
ፖ.ሳ.ቁ =2432
ኢሜል= info@ehrco.org

ሁሉም መብቶች ለሁሉም!

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ)

ኢሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፤ የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባልና የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራች አባልም ነው፡፡

# እፍታ

## ዜና




# የሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ የተሳካ እንደነበረ የኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ጥምረት ለምርጫ አስታወቀ

ገላውዴዮስ ግሩም

ኅዳር 10 የተካሄደው የሲዳማ ሕዝበ ውሳኔ በተሳካ ሁኔታ መጠናቀቁን ምርጫውን በመታዘብ የተሳተፈው የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ጥምረት ለምርጫ አስታወቀ ::

ኅብረቱ ከምርጫው በኋላ ባወጣው የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት እንደገለጸው ሕዝበ ውሳኔው ከመካሄዱ ቀደም ብሎ ምርጫውን ለሚታዘቡ አካላት አለም አቀፍ ልምድ ባላቸው ተቋማት ስልጠና መስጠቱን ገልጸዋል::

የወጣው ሪፖርት እንደሚያመለክተው በመታዘብ ሂደቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሟል:: በዚህም በረጅም እና በ አጭር ጊዜ ትዝብት ከፋፍሎ ከቅድመ ምርጫ እስከ ድህረ ምርጫ ድረስ ባለሙያዎችን አሰማርቶ ለመታዘብ ተችሏል::

ሀገራችን ባካሄደችው ህዝበ ውሳኔ በቀጣይ ሀገራችን ላይ ለሚካሄደው ሀገራዊ ምርጫ መዘጋጃ የሚሆን እና በህዝበ ውሳኔው ወቅት የታዩት ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች እንደ ግብአት መወሰድ የሚችሉ ናቸው ብሏል ሪፖርቱ::

በመጨረሻም ህብረቱ ምርጫ ቦርዱን ጨምሮ ህዝበ ውሳኔው የተሳካ እንዲሆን ለተሳተፉት በሙሉ አድናቆቱን አቅርቧል::

በተጨማሪም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) በምርጫ መታዘብ ሂደቱ ላይ በመሳተፍ በቅድመ ህዝበ ውሳኔ እንዲሁም ህዝበ ውሳኔው በተካሄደበት እለት እና ከድህረ ህዝበ ውሳኔው በኋላ ምርጫው የተሳካ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ጥምረት ለምርጫ ከ60 በላይ የሚሆኑ የሲቪል ማህበራት በግንቦት ወር 2011 ዓም የመሰረቱት እንደሆነ የሚታዎስ ነው::



ሰዋዊ

# ለጥፋት የሕዝብን ስሜት ማነሳሳት

> ይህም የሚያሳየው በዚህ ዘመን ያለው የዴሞክራሲ መንፈስ ከሰብዓዊ መብቶች መርሖዎች እየተነጠለ የመጣ መሆኑን ነው፡፡

ሱራፍኤል ግርማ


ካስ መዲ የተባለ የፖሊቲካ ሳይንስ ምሁር እ.ኤ.አ በ2004ዓ.ም The Populist Zeitgeist በሚል አርእስት ጽሑፍ አቅርቦ ነበር፡፡ ይህ ጽሑፉ የሕዝብን ስሜት በመኮርኮር ዘላቂ ያልሆነ አቋራጭ ፖሊቲካዊ መፍትሔ ለመፈለግ አዝማሚያ (ፖፑሊዝም) አዲስና ያልተንዛዛ ፍች የሚሰጥ ሆኗል፡፡ ምሁሩ በተለይም በሁለት ዕሣቤዎች ላይ ነበር ያተኮረው፡- ይህ ዓይነቱ ፖሊቲካዊ አዝማሚያ በከፍተኛ ደረጃ በስሜት በተቃኘ ዲስኩር የሚገለጽ መሆኑና በዋናነት የመራጮችን ድምፅ ለማግኘት ታሳቢ ተደርገው የሚቀረፁ ‹‹የጥቅመኛ ፖሊሲዎች››ን የሚይዝ በመሆኑ ላይ፡፡

ለግል ፖሊቲካዊ ጥቅም ሲባል የሕዝብን ስሜት መኮርኮር ከዲስኩርና ከጥቅም አነፍናፊነትም በላይ መሆኑን የሚያስረዳው መዲ፣ አዝማሚያው በደንብ በተብራራ መልኩ የቀረበ ፖሊቲካዊ ርእዮተ ዓለም ባይሆንም በጥቂት መሠረታዊ ዕምነቶች ላይ የተመሠረተ ‹‹ስስ ርእዮተ ዓለም›› መሆኑን ይገልጻል፡፡

የሕዝብን ስሜት በመኮርኮር ዘለቄታዊነት በሌላቸው ወቅታዊ ትኩሳቶች ላይ የሚያተኩሩ ፖሊቲከኞች ማኅበረሰቡን ‹‹ብዙኃኑ ሕዝብ›› እና ‹‹ልሒቃን›› በተባሉ ሁለት ተቃራኒ ምድቦች ከፍለው ነው የሚመለከቱት፡፡

» ወደ ገጽ.12 ተዛውሯል

# ከፍ ያለ ስም



ዳን ይርጋ (የሰብዓዊ መብቶችና የሕግ ከፍተኛ ባለሙያ)

## ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

እውነት ለመናገር በዚህች አጭር ጽሑፍ የኚህን ታላቅ ሰው ታሪክና ለሀገር ያበረከቱትን ሥራዎች ተንትኜ ለማቅረብ እንደማልችል ለአንባቢዎች አስቀድሜ መግለፅ ይኖርብኛል፣ እንዲሁም እንደው ዝም ከማለት በአንዲትም መሥመር ብትሆን እኚህን ታላቅ ኢትዮጵያዊ እንዲታወሱ ማድረግ ተገቢ እንደሆነ አንባቢዎች እንደሚስማሙ አምናለሁ፡፡

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም የተወለዱትና የመጀመሪያና የከፍተኛ ትምህርታቸውንም የተከታተሉት በአዲስ አበባ ውስጥ ነው፡፡ በበርካታ የውጭ ሀገራትም የተለያዩ ትምህርትን ተከታትለዋል፣ አስተምረዋል፡፡

በሐገራችን የተለያዩ ሥራዎችን አከናውነዋል፣ በሕዝብ ዘንድ በስፋት የሚታወቁት በኢሰመጉ መሥራችነታቸውና በፃፏቸው በርካታ መጻሕፍታቸው ነው፡፡ከፃፏቸው በርካታ መፅሀፍቶች ውስጥም ለመጥቀስ ያክል፡-

Atlas of Ethiopia, Geography of Ethiopia, Somalia a Child problem of Africa, Famine and drought Vulnerability፣ ጉራማይሌ፣ አገቱኒ፣ ኢትዮጵያ ከየት ወደ የት፣ መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ፣ ሰሚ ያጣ ጩኸት፣ የክህደት ቁልቁለት፣ እንዘጭና እንቦጭ ሌሎችም እንዲሁም በበርካታ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በመፃፍ ለሕዝብ አድርሰዋል፡፡

ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ያበረከቱት አስተዋጽኦ

ፕሮፌሰር መስፍን የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) ለመመስረት ሐሣብ ካመነጩና ተግባራዊ ካደረጉት አንጋፋ ምሁራን መካከል አንዱ ናቸው፡፡ ኢሰመጉን በመስከረም 29 1984 ዓ.ም. ለመመስረት የነበራቸውን ዓላማ ተጠይቀው ፕሮፌሰር ሲመልሱ «ኢሰመጉን ለመመስረት ያነሣሣን ወቅቱ የሽግግር ጊዜ እንደ መሆኑ መንግሥት የሰብዓዊ መብቶችን እንዲያከብር፣ እንዲጠብቅና ለመብቶች መከበር አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን እንዲያሟላ መንገድ ለማሳየት፣ ለማስተማርና ለማገዝ በማሰብነበር፡፡» ብለዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ታሳቢ በማድረግ የተመሰረተው ኢሰመጉ ሦስት የማይነጣጠሉ ዓላማዎች አሉት እነሱም-

1.ለሕግ የበላይነት መሥራት፣

2.ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ጥረት ማድረግና

3.ለሰብዓዊ መብቶች መከበር መታገል ናቸው፡፡

ፕሮፌሰር መስፍን ኢሰመጉን ከመመሥረትም ባለፈ ይህንን የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ተቋምን ለረጅም ጊዜ በኃላፊነትና በብቃት በመምራት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በሚገባ ተወጥተዋል፣ ይህንንም ሥራቸውን በቅርብ የሚያውቋቸውና አብረዋቸው የሠሩ ሁሉ ይመሰክሩላቸዋል፡፡ አሁንም ለዚህ ተቋም የበኩላቸውን ድጋፍና እገዛ በማድረግ ላይ የሚገኙ ጠንካራና ታታሪ ምሁር ናቸው፡፡

## አሁንያሉበትሁኔታ

ፕሮፌሰር መስፍን አሁን ዕድሜያቸው ዘጠና የደረሰ ሲሆን፣ አሁንም በኢትዮጵያ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ የነቃም ሁራዊ ተሳትፎ እያደረጉ

ይገኛሉ፡፡ ጤንነታቸው በፈቀደላቸው መጠን የተለያዩ መድረኮችም ላይ በመገኘት ጠቃሚ እውቀታቸውን፣ ልምዶቻቸውንና ትዝብታቸውን ያለማቋረጥ ለሕዝብ በማካፈል ላይ ናቸው፡፡ በተጨማሪም፣


በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በተለያዩ ጋዜጦች፣ መጽሔቶችና የፌስቡክ ገፃቸውም ላይ እስከ አሁን ድረስ ያለመታከት ያላቸውን እውቀት ለሕዝብ እያካፈሉ ይገኛሉ፡፡

## ማጠቃለያ

የ90 ዓመቱ አረጋዊ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም አልፎ አልፎ የጤና እክል ቢገጥማቸውም ሕክምናቸውን በትኩረት እየተከታተሉ እንደሚገኙና የሀገራችንንም የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ሁኔታ በትኩረት እየተከታተሉ እንዳሉ ልጠይቃቸው መኖሪያቤታቸው በሄድሁ ጊዜ ገልፀውልኛል፡፡

በመጨረሻም፡ እኔም ለእኚህ ከፍ ያለ ስም ባለቤት ታላቅ የእውቀት አባት ረጅም እድሜና ጤናን እንዲሰጣቸው ከልብ እየተመኘሁ በሌላ ጊዜ ስለርሳቸው በዝርዝርና በስፋት የተዘጋጀ ጽሑፍ እንደማቀርብ ቃል እየገባሁ ለዛሬ በዚሁ እሰናበታለሁ፡፡

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።



# ኬላ

## ሕግ

# ሕዝበ ውሳኔ እና የሕግ ማዕቀፉ በኢትዮጵያ




ጥበቡ ኃ.

### እንደ መንደርደሪያ...

ሁሉን-አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ፣ ዓለም አቀፉ የሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶች የቃል ኪዳን ስምምነት፣ የአፍሪካ የሰብዓዊና ሕዝባዊ መብቶች ቻርተር እና ሌሎችም የዓለም እና አህጉር አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች ዜጎች ሕጋዊና ምክንያታዊ ያለሆነ ገደብ ሳይጣልባቸዉ እና አድልዖ ሳይደረግባቸው በሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ በቀጥታ የመሳተፍ፣ ሃሳብ የመስጠት፣ የመምረጥና የመመረጥ መብት እንዳላቸው በተለያዩ ድንጋጌዎች እውቅና ሰጥተዋል፡፡ ይኸው የዜጎች በሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ መብት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት እና በሌሎችም የሃገሪቱ የሕግ ማዕቀፎች እውቅና ተሰጥቶት በተለያዩ ድንጋጌዎች ውሥጥ ተካትቶ እናገኘዋለን፡፡

የዜጎች በሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ የመሳተፍ መብት ሕዝብ ይወክሉኛል፣ ጥቅም እና መብቴን ያስከብሩልኛል ያላቸውን ወኪሎች በመምረጥ መብትና ጥቅሙን ማስከበር እንደሚችል እውቅና ይሰጣል፡፡ ከዚህ በተለየ መልኩ ደግሞ በአንዳንድ ወሳኝ ሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ ሕዝብ ውክልና የሰጣቸውን ተወካዮቹን ዉሳኔ በመተዉ ራሱ ሕዝቡ በቀጥታ ድምጹን በመስጠት ውሳኔውን የሚያሳልፈበት ሥርዓት ሕዝበ ውሳኔ ይባላል፡፡ በዚህ መንገድ ሕዝብ በቀጥታ ወኪል ሳያስፈልገው ውሳኔ ከሚሰጥባቸው ጉዳዮች መካከል የአዲስ ሀገረ-መንግስት ምስረታ፣ አዲስ ሕገ-መንግስት ማርቀቅ፣ የሕገ-መንግስት ማሻሻያዎች ማድረግ፣ መንግስት ለትግበራ ያዘጋጃቸውን ፖሊሲዎች በተመለከተ እና ሌሎችም መሰል የብዙሃኑን ድምጽ የሚሹ ምክንያቶች በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ በቅርቡ ካስተናገደቻቸው ታላላቅ ሁነቶች መካከል የሲዳማ ሕዝብ በክልልነት የመደራጀት ጥያቄ ማንሳቱን ተከትሎ ባለፈው ህዳር 10 ቀን 2012 ዓ.ም ተደርጎ የነበረው ሕዝበ ውሳኔ በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡ ይህም ሁነት በዓለምም ሆነ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታላላቅ ለሚባሉ አብዮቶች ጥንስስ ወይም ገፊ ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው ራስን በራስ የማስተዳደርን ሰብዓዊ መብት የማክበር እና የማስከበር ታሪክ ውስጥ በጉልህ የሚታወስ፤ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክም የተለየ ምዕራፍ የሚከፍት አጋጣሚ ሆኖ አልፏል፡፡ ምንም እንኳ ዘርዘር ያለ ትንታኔ ለመስጠት የሚያስችል በቂ መረጃዎች ማግኘት አዳጋች ቢሆንም ለዚህ ጽሁፍ ዝግጅት እንዲረዱን ያገላበጥናቸዉ የተለያዩ ሰነዶች እንደሚጠቁሙት ከሆነ ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ በአንድ ሕዝባዊ ጉዳይ ላይ ድምጽ የሰጠባቸውን አምስት ያህል አጋጣሚዎችን ማንሳት እንችላለን፡፡

የመጀመሪያው በ1979 ዓ.ም ጥር 24 ቀን በወታደራዊው ሥርዓት ደርግ ጊዜ አዲስ

ሕገ-መንግስት ለማጽደቅ ተደርጎ የነበረው ሕገ-መንግስታዊ ሕዝበ ውሳኔ ነዉ፡፡ በሕዝበ ውሳኔውም ከመቶው 81 እጅ የሚሆነው ውሳኔ ሰጪ ሕገ-መንግስቱን የተቀበለ ሲሆን ከየካቲት 19 ቀን 1979 ዓ.ም ጀምሮ ሕገ-መንግስቱ በሥራ ላይ እንዲውልና፤ በወርሃ ሃምሌ 1979 ዓ.ም የተደረገውን ጠቅላላ ምርጫ ተከተሎ ደግሞ ከመስከረም 2፣ 1980 ዓ.ም ጀምሮ የሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊት ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ መንግስት እንዲመሰረት ያስቻለ ውሳኔ የተሰጠበት ነበር፡፡

ሁለተኛው የደርግ ስርዓት መውደቅን ተከትሎ በሚያዚያ ወር 1986 ዓ.ም ኤርትራ ከኢትዮጵያ ነጻ ሆና ራሷን የቻለች ሃገር ለመሆን የቀረበውን ጥያቄ መሰረት ተደረጎ የነበረው ሕዝበ ውሳኔ ነዉ፡፡ ምንም እንኳ በርካቶች አጠቃላይ ሂደቱ ላይ ቅሬታ ሲያቀርቡ ቢሰማም በተለይም የሐገር ፍቺው ሲፈጸም የሁለቱም ሃገራት ሕዝብ በጉዳዩ ላይ ድምጹን መስጠት ነበረበት የሚለው አሁንም በበርካቶች ዘንድ አከራካሪ ሆኖ የዘለቀ ጉዳይ ነው፡፡ የሆነው ሆኖ ግን በሕዘበ ውሳኔ ውጤቱ ኤርትራ ነጻ ሀገር መሆኗ ተረጋግጦ ራሷን የቻለች ሃገር ሆና እንድትመሰረት ያስቻለ ታሪካዊ ሁነት ሆኖ አልፎ ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በብዛት ከሚሰሙት አስተያየቶች አንዱ ምናልባትም የሕዝበ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱን የተሻለ ማድረግ ቢቻል ኖሮ ኋላ ላይ ሁለቱ ሃገራት ለገቡበት እጅግ ደም አፋሳሽ ጦርነት መንስኤ ባልሆነ እና የብዙ ኢትዮጵያዊያን እና ኤርትራዊያንን ክቡር ህይወት ማዳን በተቻለ ነበር የሚለው ተጠቃሽ ነው፡፡

ሶስተኛው በህዳር 29 ቀን፣ 1987 ዓ.ም አዲስ ሕገ-መንግስት መጽደቁን ተከትሎ አዳዲስ ክልላዊ መንግስታት መመስረታቸውን ተከትሎ በተለይም የየክልሎቹን አስተዳደራዊ ወሰኖች በትክክል ለይቶ ለመወሰን ችግሮች አጋጥመው በነበሩበት የምስራቅ ሀረርጌ ቦታዎች አካባቢ በሶማሌ ወይስ በኦሮሚያ ክልል ሥር ይካለሉ የሚለውን ለመወሰን ሕዝበ ውሳኔ ተደርጎ ነበር፡፡ ምንም እንኳ የሕዝበ ውሳኔ ዉጤቱንም ሆነ ሂደቱን በትክክል የሚገልጽ መረጃ ማግኘት የጽሁፉ አዘጋጅ ያደረጉት ሙከራ ባይሳካም፤ በሂደቱ የተፈጠሩት ችግሮች ግን ዓመታትን ተሻግረው አሁንም እያነታረኩ ያሉ እና ባስ ሲልም በተለያዩ ጊዜያት ደም አፋሳሽ ግጭቶች የተከሰቱበት መሆናቸው አልቀረም፡፡

አራተኛው ከሚያዚያ 10 — 18 ቀን፣ 1993 ዓ.ም ተደርጎ የነበረው የስልጤ ብሔረሰብ ሕዝበ ውሳኔ ነው፡፡ የስልጤ ብሔረሰብ ከጉራጌ ብሔረሰብ የተለየ ማንነት ስላለው ራሱን በራሱ ሊያስተዳደር ይገባል በሚል የተነሳውን ጥያቄ መሰረት በማድረግ በተደረገው ሕዝበ ውሳኔም አስቀድሞ በጉራጌ ዞን ስር የነበረው የአስተዳደር ሁኔታ በመቀየር አዲስ የስልጤ ዞን አስተዳደር እንዲመሰረት አስችሏል፡፡




አምስተኛው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በምርጫ ቦርድ አስፈጻሚነት ከነሃሴ 17 ቀን፣ 2009 ዓ.ም - መስከረም 07 ቀን፣ 2010 ዓ.ም ድራስ የቅማንት ሕዝብ የማንነትና ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄን ተከትሎ በስምንት ያህል ቀበሌዎች የሚኖሩ ነዋሪዎች በነባሩ የዞን ወይስ በአዲስ የዞን አስተዳደር ሥር እንካለል በሚለው ላይ ድምጽ እንዲሰጡ የተደረገው ሕዝበ ውሳኔ ነበር፡፡ ይኼኛዉም ቢሆን ምንም እንኳ የድምጽ አሰጣጡ ሂደት መጠናቀቁን ተከትሎ ውጤቱ ይፋ የተደረገ ቢሆንም ከሕዝበ ውሳኔው በፊት አልፎ አልፎ ታይተው የነበሩት ግጭቶች ድህረ ሕዝበ ውሳኔ ላይ ተባብሰው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ክቡር የሰው ህይወት እንዲቀጠፍ፣ ንብረት እንዲወድም እና የከፉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት እንዲፈጸሙ በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት መሆኑ አልቀረም፡፡

እንግዲህ የሲዳማ ሕዝብ በክልልነት የመደራጀት ጥያቄ በሕዝበ ውሳኔ የሚወሰንበት እስካሁን በኢትዮጵያ ከተደረጉት ስድስተኛው ታሪካዊ ሂደት ነው ማለት ነው፡፡ ከላይ በተመለከትናቸው ሂደቶችም ሆኑ በሲዳማ ሕዝብ በክልልነት የመደራጀት ጥያቄ መነሳትን ተከትለው በተለያዩ ጊዜያት የደረሱ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ለዚህ አይነት ሂደቶች የምንሰጠው ትኩረት ከፍ ያለ መሆን እንደሚኖርበት አመላካች ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ይኸኛው የሕዝበ ውሳኔ ሂደት የሕዝብን ጥያቄ በተገቢው መንገድ መመለስ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን እና ሕዝብ በማንኛውም አጋጣሚ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች የግጭትና ሰብዓዊ መብቶች ቀውስ ሳይሆኑ በፊት በቀላሉ መፍትሄ መስጠት ተገቢ መሆኑን ያስገነዘበ አጋጣሚ ነው ማለት እንችላለን፡ ፡ በተጨማሪም እስካሁን ካደረግናቸው ሕዝበ ውሳኔዎች በመነሳት ማንኛውም ጥያቄዎች ከሕዝብ ሲነሱም ሆነ መፍትሄ ሲሰጣቸው ሕዝብን በንቃት ያሳተፈ፣ ለሀገሪቱ የዲሞክራሲዊ ስርዓት ግንባታ በሚበጅ መልኩ ይሆን ዘንድ በቂ የሚባል ልምድ መቅሰም ተገቢ ነው፡፡

## ሕገ-መንግስቱ ስለ ሕዝበ ዉሳኔ

የ1987 ዓ.ምቱ የኢ.ፌ.ደሪ ሕገ-መንግስት በሦስተኛዉ ምዕራፍ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ለብሔሮቸ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸዉን በራሳቸው የማስተዳደር ሙሉ መብት ያጎናጽፋቸዋል፡ ፡ ዝቅ ብሎ በሚገኘውና የፌደራል መንግስቱን አባላት በሚዘረዝርበት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ደግሞ እነዚሁ ብሔሮቸ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብታቸውን በመጠቀም ባሻቸዉ ጊዜ የራሳቸዉን ክልል የመመስረት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ ይህንን መብት ለመጠቀም ሕገ-መንግስቱ አስፈላጊ ናቸው ብሎ በቅደም ተከተል ያስቀመጣቸው ሥነ-ሥርዓቶች አሉ፡፡

በቅድሚያ ጥያቄው የቀረበለት የሚመለከተው የብሔሮቸ፣ ብሔረሰቦች ወይም ሕዝቦች ምክር ቤት ጥያቄዉን ተቀብሎ 2/3 በሆነ ድምጽ ካጸደቀው ለሚመለከተው የክልሉ ምክር ቤት ጥያቄውን በጽሁፍ ያቀርባል፡፡ የክልሉ ምክር ቤት ጥያቄውን በተቀበለ በአንድ አመት ያህል ጊዜ ውስጥ የቀረበውን ጥያቄ በተመለከተ ሕዝበ ዉሳኔ እንዲደረግ ይመራል፡፡ የክልልነት ጥያቄዉ በሕዝበ ውሳኔዉ በአብላጫ ድምጽ ድጋፍ ያገኘ ሲሆን እና የቀድሞው ክልል ምክር ቤት ሥልጣኑን ጥያቄውን ላቀረበው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሲያስተላልፍ ሌላ አይነት ማመልከቻ ሳያስፈልግ አዲስ የተመሰረተው ክልል በቀጥታ የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል በመሆን

» ወደ ገጽ.13 ተዛውሯል

# ቀለም

## ሥነ_ጽሑፍ

# ተ.....መ.....ዘ.....ኑ.....!!!

ጥበቡ ኃ.

ከወትሮው የተለየ ምንም ነገር የለም፡፡ ሁሉም ያው ሁሉም የነበረ ነው፡፡ ህይወት “ባለህበት እርገጥ” ከሆነች ሰነባበተች፡፡ የሚቀየር ቢጠፋ የምገባና የምወጣበትን መንገድ እየቀያየርኩ ራሴን ለውጥማ አለ እያልኩ መንገር ከጀመርኩ ከራረምኩ፡፡ “አንተ ማነህ..?” ለሚል ራሴን እንዳልገልጥ፣ ራሴን እንዳላውቅ ሆኜ ያደግኩ ነኝና እኔ’ን መግለፅ ብችል የሚሰማኝን ደስታ ሳስበው እራሱ ያሰክረኛል፡፡ ይኸን ስንፍናዬን ግን ቢያንስ እኔ ማለት የዚህ ትውልድ አንዱ ቁጥር ነኝ ብዬ አድበስብሼው ብቀጥል እመርጣለሁ...፡፡

አመሻሹ ላይ በተማሪዎች መግቢያ በር በኩል ዘወትር የማይቀረው ግርግር ዛሬም በቦታው አለ፡፡ ወደ ቤተክርስትያን የሚሄዱ፣ ራት ሊበሉ ወይ ቡና ሊጠጡ ከግቢ የሚወጡ ተማሪዎች፣ እፍኝ ለማትሞላ ደሞዝ ረዥም መንገድ አቆራርጠው ወደ ቤታቸው የሚቻኮሉ የኢንደስትሪ ፓርክ ሰራተኞች፣ ከስራ ቦታ ወደ ቤት የሚጣደፉ ሰዎች... ሁሉም በየፊናቸው ይሮጣሉ፡፡ ከአላፊ አግዳሚዎቹ መሃል ከፊሎቹ ሰብሰብ ብለው ይሆነ ነገር ይሰማሉ... ሃዋሳ ጎዳናዎች ላይ በብዛት የተለመደው የመንገድ ዳር ስብከት ይሆናል በሚል ብዙም ልብ ሳልለው፤ ከጆሮ ማዳመጫዬ የሚሰማኝን ሙዚቃ እያጣጣምኩ እግሬን አፍታታለሁ፡፡




የተሰበሰቡትን ሰዎች አልፌ ከመሄዴ በፊት በአይኔ ብዞር “...ያመዋል...!? ጤነኛ አይደለም...!?” እያሉ የሚጠቋቆሙ የጎን ራስ ቅላቸውን በሌባ ጣታቸው እየጠነቆሉ የሚያሽከረክሩ ሰዎችን በብዛት አያለሁ፡፡ ለአፍታ ቆም ይሉና ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁ ጣታቸውን ራስ ቅላቸው ላይ እያሽከረከሩ ጉዞ ይቀጥላሉ፡፡ ከእግሬ ዘገም ብያለሁ በአንዱ ጆሮዬ ያለውን ማዳመጫ ነቅዬ ጆሮዬን ሰብሰብ ወዳሉት ሰዎች ተክያለሁ... አልፎ የሚመጣው ድምፅ ይሰማኛል...

“...እያንዳንድሽ ብትመዘኝ ይሻልሻል... ኪሎሽን በጊዜ እወቂ... ምንም የሚያስፈራ ነገር የለውም... ትውልድ ይሳሳታል፤ ትውልድ ይታረማል... አትፍሩ ኑ ተመዘኑ...!!”

ለወትሮው ህፃናት ልጆች የሚያዟት ትንሿን ሚዛን እግሩ ስር አስቀምጧል... ግፋ ቢል እድሜው ከሃያ አምስት የማይዘል ቀጭን ለግላጋ ወጣት ነው... ገፁ በእድፍ ብዛት ወይቧል፤ ልብሶቹ ገላውን በቅጡ ቢሸፍኑም ድርት ስለበዛባቸው እርጅናቸው በግልፅ ይታያል፡፡ የቀለም ባሊ ባፉ ደፍቶ ቂጡ ላይ ተቅምጦ በእጁ የያዛትን ሳንቲም ከሚዛኗ ጋር እያነቀጫቀጨ፤ በል ሲለው ደግሞ ቆሞ እጆቹን እያወናጨፈ ይሳደባል፣ ይወቅሳል፣ ያሞግሳል፣ ይስቃል፣ በምሬት ይጮሃል...

“...ቃ ቃ ቃ... ተመዘኑ... ኑ ተመዘኑ...”

“... ኑ እንጂ ተመዘኑ... ራሳችህን መዝኑ፤ ራሳችሁን ለኩ፡፡ የት ነበርን..? አሁን የት ነን..? ወዴትስ ነን..? ብላችሁ ጠይቁ... እመኑኝ በብዙ የምታተረፉት እናንተዉ ናችሁ፡፡ ለኔ የምትሰጠኝ አምሳ ሳንቲም እንደሁ ዳቦ እንኳን አይገዛልኝም፡፡ አንተ ግን ኪሎህን ታውቃለህ፤ ከእንቅልፍህም ትነቃለህ፡፡ መመንመንህ፣ መቀንጨርህ፣ መከሳትህ ሲገባህ መባነንህ አይቀርም... ቁመትህ እና ኪሎህ እንደማይመጣጠኑ ስለምታውቅ ታፍራለህ፤ ትሸማቀቃለህ፡፡ ትላነትህ፡- ዓለምን ያስደመመ የድንቅ ስልጣኔ ራስነት፣ ዛሬህ፡- ነፍስህን ማቆያ ጥሬ ከነጭ እጅ የምትጠብቅ ብኩን ምንዱባንነት፣ ነገህ፡- ዉል የጠፋዉ ደንባራነት መሆኑ ትዝ ሲልህ ይቆጭህ ይሆናል፡፡ ያኔ መላው አፍሪቃ፣ መላው ጥቁር ሕዝብ ጨለማ በለበሰበት ዘመን የነፃነት ቀንዲል ለኳሽ መሆንህን ስታስታውስ እና ዛሬ ቀን ተገልብጦ ለቀዬህ እና ለመንደርህ ሕዝብ ነፃነት እየታገልኩ ነው ስትል ማፈርህ አይቀርም፡፡ እኔንኮ የሚገርመኝ ‘ማን’ን ከማን ነው ነፃ እንደምታወጣው ነዉ..!?’ አለማፈርህ!?”

“ኢትዮጵያውያን እኮ ዶጋሊና መቀሌ፣ አምባላጌና አድዋ ላይ ነፃ ወጥተዋል... ይልቅ ራስህን ወንዝህን እያሰብክ እንድትኖር ካረገህ ሸባ አስተሳሰብ ነፃ አድርግ... ራሱን ነፃ ያላወጣ ነፃ አውጪ ነፃነትን እሰጠወለሁ ለሚለው ሕዝቡ ባርነትን እንጂ ነፃነትን አይሰጠውም አለ ያ ፖልታኪ....”

ወጣቱ ሰው እረፍት እንኳ አይወስድም፡፡ ጣቶቹን ከፊት መስመር አከባቢ ካሉት የዩንቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ እያወዛወዘ...

“...የእናንተ ትውልድ መመዘን አለበት፡፡ ኪሏችሁን ማወቅ አለባችሁ፡፡ ችግሩ ሚዛን ትፈራላችሁ... እጃችሁን አጣምራችሁ ጠብመንጃ ፊት እንዳልቆማችሁ... ኑ ተመዘኑ ስትባሉ ትሸሻላችሁ፡፡ እያንዳንድሽ ስራሽን ታወቂያለሻ! እንዴት አትፈሪ። ስራ ጠፋ እያልሽ ድንጋይ ላይ የምትጎለቺው አንቺ፣ ራስህን በሱስ አፈር ምስህ የቀበርከው አንተ፣ ውጣ ስትባል የምትወጣው ግባ ስትባል የምትገባው ተነስ ቢሉህ ተቀመጥ ‘ለምን’ እንኳ ብለህ የማጠይቀው አንተ እንጂ ማን ሌላ ይመጣልሃል፡፡ አዎ! ተመዘኑ ስትባሉ ፊታችሁን ታዞራላችሁ በዘር ቆጠራ፣ በሃይማኖት፣ በወንዝ እና በቀዬ ራስህን ስትሸነሽን ስለከረምክ ተመዘን ስትባል እንዳትቀል፣ ከኪሎ በታች እንዳትሆን ትፈራለህ... ወደህ አይደለም የምትፈራዉ... አይቼሃለሁ ትላንት በየዩንቨርሲቲው ዱላ ይዘህ ስታዘጠዝጥ፣ አይቼሃለሁ ተራ የልጆች ፀብን ወደ ብሔር ፀብ ለውጠህ አገር ስታሸብር፣ አይቼሃለሁ ግንባሩን ስማ የላከቺዉን ልጇን ግንባሩን ደፍተህ ሬሳ ስትልክላት... “

እሱ እራሱ ወጣት ሆኖ እኩዮቹን እንዲህ ሲወርፍ ማየቴ አስገርሞኛል፡፡ አንተስ ምን አድርገሃል ለማለት ጉሮሮዬን ስጠራርግ፤ እሱ ቀድሞኝ መናገር ጀምሯል...

“እኔ ላይ አታፍጥ... እኔም ግራ ቢገባኝ ነው የምለፈልፈዉ...

ቀውስ ምናምን እንዳልመስልህ... እኔም እንዳንተው ዩንቨርሲቲ ተማሪ ነበርኩ... ጨርሼ ድንጋይ ላይ መቀመጥ ቢሰለቸኝ ነዉ ይቺን ሚዛን ይዤ የምዞረው፡፡ እሺ! አያሳስብህ እኔ እብድ ነኝ! ከእነ እብደቴ ተወኝ...! ግን ቢያንስ በምለው አትሳቅ፣ አታሽሟጥ፣ እውነት አልተናገርክም ካልክ ና ሞግተኝ፡፡ ይኸኛው ትውልድ ያለፈውን፣ ያለፈው ያ’ን ትውልድ፣ ያ ትውልድ የቀደመውን ሲወቅስ ስንወቃቀስ እድሜያችንን እንጨርሳለን፡፡ እሽክርክሪቱ ይሆነ ቦታ ላይ ሊያቆም ግድ ይለዋል፡፡ አንዱ መጥቶ ሌላው በሄደ ቁጥር ኢትዮጵያን የሚያንገዳግዳት በሽታ አሁን፣ በኛ ዘመን፣ በእኛ ጊዜ ሊያበቃ የግድ ነው፡፡ እኛ የአባት እናቶቻችን መልካም ታሪኮች ትሩፋት ነን፡፡ ኢትዮጵያ በኛ ዘመን አትከሸፍም፡፡ ይኼን ዘመን በሚመጥን ሃሳብ ኢትዮጵያን ዳግም የነበረችበትን ከፍታም አልፈን የኛን ዘመን ድንቅ ታሪክ እኛው እንፅፋለን፡፡ ለዚህ ሁላችንም ድርሻ እንወስዳለን፡፡ ተነሱ፡- ስለተባልን አንነሳም፣ ውጡ፡- ስለተባልን አንወጣም፣ ፍለጡ ቁረጡ ስለተባልን ያንን አናደርግም፤ ስለ ነገይቱ ኢትዮጵያ ስለምናስብ በምናወራው በምንሰራው በመንገዳችን ሁሉ ትልቋን ቤት አስበን እንሄዳለን...”

ወጣቱ ሰው ፊት ላይ የሚታየው ደስታ አንዳች የተስፋ ስሜት አጋባብኝ፤ እውነቱን እኮ ነው... እንዴት ኢትዮጵያ በኛ ዘመን ትከሽፋለች፣ ምን ስንል እንፈቅዳለን፡፡ ይኸን ከራሴ ጋር ሳወራ ወጣቱ ሰው ሚዛኑን ብብቱ ስር ሸጉጦ የቀለም ባሊውን በእጁ አንጠልጥሎ ተነስቶ እየሄደ ነበር፡፡ አጠገቤ እያለ ልብ ያላልኩት ወጣቱ ሰው ሲራመድ ከእግሩ አንከስ ይላል፡፡ ብብቱ ስር የሸጎጣት ሚዛን አስር ግዜ ከብብቱ እየተንሸራተተች በእጁም ከፍ እያረጋት አንገቱን አጎንብሶ ወደ ፊቱ ደፋ ደፋ እያለ ሲሄድ፤ ኢትዮጵያም በታሪኳ በእንዲህ ያለ ከፍታና ዝቅታ ብታልፍም በብብቷ የያዘቻቸው ሚዛን ጠባቂ ልጆቿ እንዳያመልጧት በጠንካራ ክንዷ፣ ባላትም በሌላትም እያስተማረች እዚህ ያደረሰቻቸው ልጆቿ ወደ ቀደመው ክብሯ፤ ካለፈውም ወደ ላቀ ከፍታዋ እናደርሳታለን...! እንደ ትዉልድ ብንመዘን እንዳንቀል፣ እኔም ሚዛን ላይ ብወጣ ቀልዬ እንዳላፍር እኔ ሃገሬን በሃላፊነት ወስጃለሁ፡፡ እናንተስ!?

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

» ከ ገጽ.5 የዞረ

# ለጥፋት የሕዝብን......

ለተከታዮቻቸውም የሚሰብኩት ‹‹ብዙኃኑ ሕዝብ›› በመሠረቱ መልካም፣ ‹‹ልሒቃን›› ደግሞ በመሠረቱ የነቀዙና ከሕዝቡ የዕለትተዕለት ሕይወት የራቁ መሆናቸውን ነው፡፡ በሕዝቡ ውስጥ ለማሥረፅ የሚሞክሩት ሌላኛው ዕሣቤ ደግሞ ፖሊቲካ ‹‹የብዙኃኑ ፈቃድ›› ነጸብራቅ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ይህን አዝማሚያ አደገኛ የሚያደርገው ማኅበረሰባዊ ክፍፍሉ የሚመሠረተው በማንነት እንዲሁም በ‹‹ወገን›› እና በ‹‹ጠላት›› መካከል ‹‹አለ›› ተብሎ ከሚታሰበው ግልጽ ልዩነት በሚመነጭ ስሜት ላይ መሆኑ ነው፡፡ እንዲህ ባለው ፖሊቲካዊ አዝማሚያ የውይይት መድረኮች ሁሉ በልሒቃን ቁጥጥር ሥር መሆናቸው ስለሚታመን ድርጊቶች የሚገለጹት በትንኮሳና በዐመፅ ነው፡፡

ለመሆኑ የሕዝብን ስሜት በመኮርኮር ዘለቄታዊነት በሌላቸው ወቅታዊ ትኩሳቶች ላይ የማተኮር ፖሊቲካዊ አዝማሚያ መንሥዔዎች ምንድር ናቸው?

❖የወጣቶች ሥራ አጥነት የሚፈጥረው ቀቢፀ ተስፋ፣

❖በኅብረተሰቡ ውስጥ እየጎላ የሚመጣ የገቢ ልዩነት፣

❖መንግሥታዊው ሥርዓት የራሱን አጀንዳና ፍላጎቶች እውን ለማድረግ ከመጣር በቀር የዜጎችን ድምፅ እንደማይሰማ መደምደም፣

❖በነባር የፖሊቲካ ፓርቲዎች ላይ ዕምነት ማጣት፣

❖የብዙኃኑን ቀልብ መግዛት የሚችሉ፣ በጣም በቀላሉ የሚሳኩ የሚመስሉ የአቋራጭ መፍትሔዎችን የሚያቀርቡና የፖሊቲካ ተቀናቃኞቻቸውን የሚያራክሱ ወትዋቾች መከሰት ናቸው፡፡

የሕዝብን ስሜት በመኮርኮር ወቅታዊ ትኩሳት የመፍጠር ፖሊቲካዊ አዝማሚያ ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መንሥዔ ሲሆን በተደጋጋሚ ታዝበናል፡፡ የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶች ዕሣቤዎች በዳበሩባቸው ምዕራብ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ እንኳ ሳይቀር ለናዚ/ ፋሺዝም አስተሳሰብ የቀረበ አደገኛ ዐቋም የሚያንጸባርቁ ቀኝ ዘመም የፖሊቲካ ፓርቲዎች በምርጫ አሸንፈው ወደ ሥልጣን እየመጡ ናቸው፡፡ እነዚህ ፓርቲዎች የብዙኃኑን ድጋፍ ለማሰባሰብ የቻሉበት የጸረ ስደተኞች ዐቋም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ የሰብዓዊ መብቶችን በማስከበረ ረገድ የተመዘገቡ ስኬቶችን እንዳይቀለብስ አሥጊ ሆኗል፡፡

በእኛም ሐገር የበቀሉ አክራሪ ብሔር ተኮር ፖሊቲከኞች የሕዝብ ድጋፍ ለማሰባሰብ ከሚጠቀሙባቸው መቀስቀሻዎች አንዱ ‹‹የመጤ›› እና ‹‹የተወላጅ›› ትርክት ነው፡፡ በፖሊቲካ ዕውቀታቸው ያልበሰሉ ጮርቃ ወጣቶችን በየብሔራቸው በማደራጀት ‹‹ጠላት›› ተደርገው በተሣሉ ወገኖች ላይ ጥቃት



እንዲያደርሱ በመቀስቀስ በተለያዩ አካባቢዎች ከባድ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል፡፡ መሬት ዋነኛ የኢኮኖሚና የፖሊቲካ ቁጥጥር መሣሪያ በሆነባት፣ ከአጠቃላይ ሕዝቧ ሰማንያ በመቶ ያህሉ የገጠር ነዋሪ በሆነባት እንዲሁም ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄዎች ‹‹ከአገር/መሬት ባለቤትነት›› ተለይተው በማይታዩባት ኢትዮጵያ ‹‹የመጤ›› እና ‹‹የተወላጅ›› ትርክት ብሔር ተኮር ገጽታ ተላብሶ ለሚሊዮኖች መፈናቀል፣ ለብዙዎች ሕይወት መጥፋትና ለንብረት ውድመት ምክንያት ሆኗል፡፡

‹‹ህዩማን ራይትስ ዎች›› እ.ኤ.አ በ2017ዓ.ም በዓለም ሐገራት ያለውን የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ሁኔታ ይፋ ባደረገበት መግለጫ ላይ የድርጅቱ ኤግዝክዩቲቭ ዳይሬክተር ኬኔት ሮዝ The Dangerous Rise of Populism በሚል አርእስት ባቀረበው ጽሑፍ የቀኝ ዘመም ፖሊቲካን አደገኛነት ተንትኗል፡፡ የሕዝብን ስሜት በመቀስቀስ ወቅታዊ የፖሊቲካ

ትኩሳት የሚፈጥሩ ፖሊቲከኞች ሰብዓዊ መብቶችን የሚመለከቱት እነርሱ ለሚያቀነቅኑት «የብዙኃን ፈቃድ» እንቅፋት አድርገው መሆኑን የሚገልጸው ኬኔት ሮዝ፣ ሰብዓዊ መብቶች ሰዎች ሁሉ የሚጎናጸፏቸው የመሆናቸውን እውነታ እንደማይቀበሉም ያስረዳል፡፡ «ሰዎች፤ መብቶችን በተመረጠ ሁኔታ ማስከበር ይቻላል በሚል አደገኛ ግምት - ማለትም፣ የራሳቸው መብት እስካልተነካ ድረስ የሌሎች መብት ሊጣስ እንደሚችል በማሰብ ይጽናናሉ፡፡» የሚለው የሰብዓዊ መብቶች ተከላካዩ መብቶች ግን በባሕርያቸው ሳይነጣጠሉ አንድ ላይ የሚወሰዱ እንጂ እንደ ሆቴል ምግብ ከገበታ ዝርዝር ላይ የሚመረጡ አለመሆናቸውን ያስታውሳል፡፡

ኬኔት ሮዝ ትንታኔውን በመቀጠል «ጎረቤቶችህን አትወድዳቸው ይሆናል ነገር ግን ዛሬ የእነርሱን መብት መሥዋዕት ካደረግህ ነገ አንተም ተመሳሳይ ዕጣ ይደርስብሃል፤ ምክንያቱም መብቶች የተመሠረቱት አንተ እንዲደረግልህ የምትፈልገውን ለሌሎች ማድረግ እንዳለብህ በሚያሳስብ ብድር የመመለስ ዕሣቤ ላይ ነውና፡፡ የተወሰኑ ወገኖችን መብቶች መጣስ በአሁኑ ሰዓት በስማቸው የመብት ጥሰት እንዲፈጸም ምክንያት ለሆኑ ‹ብዙኃን› የኋላ ኋላ አስፈላጊ የሆኑ መሠረቶችን መናድ ነው፡፡» ሲል ያስጠነቅቃል፡፡

በደቡብ ምሥራቅ እስያ ጥናት ላይ የተሠማራው ቦን ጁዌን የፊሊፒንሱ ፕሬዚደንት ዱቴርቴ «የብዙኃኑን ፈቃድ» በመፈጸም ሰበብ የሚያደርሷቸውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በተነተነበት ጽሑፍ እንደገለጸው ብዙዎቹ ፖሊቲከኞች ቢያንስ ለይስሙላም ቢሆን በሁሉን አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች ተገዥ መሆናቸውን ይናገራሉ፤ እንደ ዱቴርቴ ዓይነቶቹ ዓምባ ገነኖች ግን ዋነኛ ባሕርይአዊ መገለጫ በሰብዓዊ መብቶች ተቋማትና ዕሣቤዎች ላይ የሚፈጽሟቸው ጥቃቶች ናቸው፡፡

ብዝኃነትን በራሱ ለዓላማቸው መሳካት እንቅፋት አድርገው የሚወስዱት ለጊዜአዊ ጥቅም ሲሉ የሕዝብን ስሜት የሚኮረኩሩ ፖሊቲከኞች «እንወክለዋለን» የሚሉትን ወገን ጥቅም በማስከበር ሽፋን ማንኛውንም ዓይነት የዘር አድልዎ ለማስወገድ የተደረገውን ዓለም አቀፍ ስምምነት ከመጣስ ወደ ኋላ አይመለሱም፡፡ የእንዲህ ዓይነቶቹ ፖሊቲከኞች ዲስኩርና ተግባር ዋና ማጠንጠኛ የሰብዓዊ መብቶች ዕሤቶች መሠረቶች የሆኑትን ሁሉን አቀፍነት፣ የማይነጣጠሉና የማይገሠሡ የመሆናቸውን እውነታ የሚጻረር ነው፡፡ ሰሞኑን እንዳስተዋልነው ተጨባጭ የፖሊሲ አማራጭ ከማቅረብ ይልቅ ለጊዜአዊ ጥቅም ሲሉ የሕዝብን ስሜት የሚኮረኩሩ ፖሊቲከኞች በሕዝብ መካከል ብሔርንና ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች በመቀስቀስ ከፍተኛ ጉዳት የማድረስ ዐቅም አላቸው፡፡

በአውሮፓና በአሜሪካ ሲሆን እንዳየነው የሕዝብን ስሜት በመቀስቀስ ወቅታዊ ትኩሳት የሚፈጥሩ ፖሊቲከኞች ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ግድ እንደማይሰጣቸው በይፋ እየተናገሩ እንኳ በሰፊ ልዩነት በምርጫ አሸናፊ ሆነው ሥልጣን ይዘዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው በዚህ ዘመን ያለው የዴሞክራሲ መንፈስ ከሰብዓዊ መብቶች መርሖዎች እየተነጠለ የመጣ መሆኑን ነው፡፡ ስለሆነም፣ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካዮችና ፖሊቲከኞች ወደ ችግሩ ሊመሩ የሚችሉ ሥነ ልቡናዊ፣ ፖሊቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁናቴዎችን በማጥናት መፍትሔ የሚያመጡ ሥልቶችን መቀየስ ይገባቸዋል፡፡

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።

» ከ ገጽ.9 የዞረ

# ሕዝበ ውሳኔ

በንዑስ አንቀጽ 3 ሥር በተዘረዘረው መሰረት ሂደቱ የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡

## አዲሱ የምርጫ፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና ሥነ-ምግባር ዐዋጅ ስለ ሕዝበ ዉሳኔ

ባለፈው አመት 2011 ዓ.ም መጨረሻ አዲስ የምርጫ፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና ሥነ-ምግባር ዐዋጅ መጽደቁ ይታወሳል፡፡ ዐዋጁ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ልዩነት ሳይደረግባቸው ነፃ፣ ፍትሃዊ፣ ሰላማዊና ቀጥተኛ በሆነ ምርጫ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ሕገ-መንግስታዊ ስልጣናቸውን ተግባር ላይ እንዲያውሉ፣ ዜጎች ሁሉአቀፍ፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጢር ድምፅ አሰጣጥ ፈቃዳቸውን በነፃነት የሚገልጹበት ምርጫ ላይ የመሳተፍ መብታቸው እንዲረጋገጥና የመደራጀት መብታቸውም እንዲጠበቅ ለማስቻል ታሳቢ ተደርጎ መዘጋጀቱ በመግቢያው ላይ ተገልጧል፡፡

ዐዋጁ በአንቀጽ 6 ላይ በኢትዮጵያ የሚካሄዱ የምርጫ አይነቶች አምስት እንደሆኑ ያስቀምጣል፡፡ እነሱም የአካባቢ ምርጫ፣ የጠቅላላ ምርጫ፣ የማሟያ ምርጫ፣ የድጋሚ ምርጫ እና ሕዝበ ውሳኔ ናቸው፡፡ በዐዋጁ የትርጉም ክፍል ስር ሕዝበ ዉሳኔ ምን ማለት እንደሆነ ትርጉም ያስቀመጠ ሲሆን፤ በሕገ-መንግስቱ መሰረት ውሳኔ ሲሰጥ የህዝብ ፍላጎትን ለመለካት እና የህዝብን ውሳኔ ለማወቅ ድምፅ የሚሰጥበት ስርዓት ነው በማለት ይገልጽዋል፡፡ የዐዋጁ አንቀጽ 11 ምርጫ ቦርድ በሕገ-መንግስቱ መሰረት አግባብ ባለው አካል ተወስኖ ሲቀርብለት የህዝብን ፍላጎት ለመለካት ወይም ለመወሰን ድምጽ እንዲሰጥ ህዝበ ውሳኔ የሚሰጥበት ምርጫ እንደሚያዘጋጅ ይደነግጋል፡፡

የሲዳማ ሕዝብ በክልልነት የመደራጀት ጥያቄ በዋነኝነት የሚመለከተዉ የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ሲሆን በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 3 በተዘረዘረዉ መሰረት የክልልነት ጥያቄው ከሚመለከተው፡- ማለትም ከሲዳማ ዞን ምክር ቤት ሲቀርብለት፤ በጉዳዩ ላይ ሕዝበ ውሳኔ እንዲደረግ ለሚመለከተው የምርጫ አስፈጻሚ አካል ማለትም ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በማስተላለፍ እንዲፈጸም ያደርጋል ማለት ነው፡፡ ቦርዱም ህዝበ ውሳኔው እንዲካሄድ የወሰነው አካል በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ህዝበ ውሳኔው ያስፈለገበትን ጉዳይ ለመለየት በሚያስችለው መልኩ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን በማደራጀት ህዝበ ውሳኔውን ያከናውናል፡፡

በዚህ መልኩ የሚጀምረዉ የሕዝበ ውሳኔ ሂደቱ ዝርዝር አፈጻጸሙ ቦርዱ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ እኛም የሲዳማ ሕዝብ በክልልነት የመደራጀት ጥያቄን ለመመለስ ያለፈው ሕዳር 10 ቀን፣ 2012 ዓ.ም የተደረገውን ሕዝበ ውሳኔ አስመልክቶ ያዘጋጀነውን በኢትዮጵያ የሕዝበ ውሳኔ ለማስፈጸም የሚረዱ የሕግ ድንጋጌዎችን በአጭሩ ለመዳሠስ የሞከርንበትን ጽሁፍ በዚሁ እናጠናቅቃለን፡፡

ይህ ጽሑፍ የጸሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው።